# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

### የዓቢይ ጾም አምስተኛው ሰንበት «ደብረ ዘይት» ይባላል።

## የዕለቱ ምስባክ

እግዚአብሔርሰ ገሀድ ይመጽእ
ወአምላክነሂ እያረምም
እሳት ይነድድ ቅድሜሁ

እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል
አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም
እሳት በፊቱ ይቃጠላል (ይነዳል)

መዝ ፵፱(፶)፥፫

ትርጉም፥ የተሰበከው ምስባክ ሁለቱን የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአቶች የሚያስገነዝበን ነው።

- እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ማርያም የማርያምን ሥጋ ለብሶ ይመጣል፤ መጥቶም ዝም አይልም (አሌ ለክሙ ጸሐፍት ወፈሪሳውያን መደልዋን - ግብዞች ጸሐፍት ፈሪሳውያን ወዮላቸው) እያለ ይወቅሳል ወንጌልንም ያስተምራል።
- እግዚአብሔር ወልድ በክበበ ትስብእት በግርማ መለኮት ሁለተኛ ይመጣል። መጥቶም ዝም አይልም ጻድቃንን «እናንተ የአባቴ ብሩካን ወደ እኔ ኑ » ብሎ ይጠራል። ኃጥአንንም «እናንተ እርጉማን ከዚህ ወግዱ» ብሎ ያሰናብታቸዋል።

በፊቱ እሳት ይነዳል ማለት ጻድቃን የሚድኑበት ሕይወት ኃጥአን የሚጠፉበት መዓት በባሕርዩ አለ ማለት ነው።

ወንጌል፥ ማቴ ፳፬፥፩-፴፮
ቅዳሴ፥ የአትናቴዎስ

## የዕለቱ ትምህርት

Ä , V ¶Â‰

ደብረ ዘይት ማለት የወይራ ዛፍ ያለበት ተራራ ማለት ሲሆን ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ ጥቂት ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ የሚገኝ ተራራ ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ዳዊት ከአቤሴሎም በሸሸ ጊዜ የደብረ ዘይትን አቀበት እንደወጣ (፪ኛ ሳሙ ፲፭፥፴) ላይ እናነባለን። ዘሩባቤል ከሠራው ቤተ መቅደስ አደባባይ ደብረ ዘይት ሰባ አምስት ሜትር ገደማ ከፍ ብሎ ይገኛል። ቤተ ፋጌና ቢታንያ የሚባሉት ታሪካውያን ቦታዎች ከደብረ ዘይት ግርጌ ይገኛሉ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሆሣዕና ዕለት ከደብረ ዘይት ወደ ኢየሩሳሌም እንደገባ (ማር ፩፥፲፩) እናነባለን።

ጌቴሴማኒ የሚባለው ጌታችን የጸለየበት ቦታ ከደብረ ዘይት ስር ይገኛል (ማቴ ፳፮፥፴-፴፮)። ጌታችን ወደ ሰማይ ያረገው በደብረ ዘይት ላይ ነው (ሉቃ ፳፬፥፶፪ ። ሐዋ ፩፥፲፪)። መድኃኒታችን በደብረ ዘይት ተራራ በዓለም ፍጻሜ ዓለሙን ለማሳለፍ እንደሚመጣ ተተንብዮአል (ዘካ ፲፬፥፬)። መድኃኒታችንም ነገረ ምጽአቱን (ዳግም ምጽአቱን) በደብረ ዘይት ተራራ ላይ በሰፊው አስተምሯል (ማር ፲፫፥፫)።

በመሆኑም ፭ኛው የዓቢይ ጾም ሰንበት የክርስቶስ ነገረ ምጽአት የሚዘመርበት የሚሰበክበት ዕለት ስለሆነ በደብረ ዘይት ተሰይሟል። ስያሜው የቅዱስ ያሬድ ነው

ይህ ዕለት ደብረ ዘይት ይባላል። ስያሜው እንደቀደሙት ሰንበታት ሁሉ የቅዱስ ያሬድ ስያሜ ሲሆን በዚህ ቀን መድኃኒታችን ሁለተኛ በግርማ መለኮት በክበበ ትስብእት (በመለኮታዊ ግርማው በሰው መጠን) እንደሚመጣ የዓለምም ፍጻሜው እንዴት እንደሚሆን ለሐዋርያት በደብረ ዘይት ማስተማሩን እንዲሁም በክብር ያረገው ጌታን ለሚጠባበቁት ዋጋቸውን ላልተቀበሉትም ፍዳቸውን ሊከፍል የምድርን ሥርዓት ሊሽር ሰማይና ምድርን አሳልፍ ለወዳጆቹ መንግሥቱን ሊያወርስ የቅዱሳኑንም እንባ ከዓይናቸው ሊያብስ ኃጥአንን ሊወቅስ ጻድቃንን ሊያወድስ (ብሩካን ብሎ) መምጣቱን እያሰበች ቤተ ክርስቲያን ፈጣሪዋን ታመልካለች። ቅደስ ያሬድም ይህንኑ ትምህርት በመዝሙሩ ጠቅሶ ስለዘመረውና በዚህ ቀንም እንዲዘመር ስለተደረገ ዕለቱ በባለዜማው ይትበሃል ደብረ ዘይት ይባላል።

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

እንዘ ይነብር እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት
(ጌታችን በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ)

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ተሰሎ ፬፥፲፫ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፪ኛ ጴጥ ፫፥፯-፲፭ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፬፥፩-፳፪ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

በዚህ ዕለት የሚነበበው የወንጌል ክፍል ማቴዎስ ፳፬፥፩-፴፮ ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቅደስ ወጥቶ ወደ ደብረ ዘይት በሄደበት ሰዓት ደቀመዛሙርቱ አጠገቡ ቀርበው ዘሩባቤል ያሳነጸውን የመቅደስ ግንቦች እያሳዩት ሳለ «እውነት እላችኋለሁ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም» አላቸው። ከዚህ በኋላ የኢየሩሳሌምን መፍረስ የእርሱን ዳግም መምጣት አስፍቶ አምልቶ ከነምልክቱ አስተማራቸው።

### የዓለም መጨረሻ የኢየሱስ ክርስቶስ መምጫ ምልክቶች፥

፩) ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በክርስቶስ ስም ብዙዎችን ያስታሉ። (ማቴ ፳፬፥፬-፭)

፪) የጦርነት ወሬ የዓለምን ዜና ያጣብባል በዓለም ዙሪያም ሰፊ ጦርነት ይደረጋል፤ የጦርነትንም ወሬ ፍጥረት ሁሉ ይሰማ ዘንድ ግድ ነው። ክርስቲያኖች ግን በዚህ ጊዜ የክርስቶስን መምጣት ሊጠብቁ እንጂ ሊደነግጡ አይገባም። (ማቴ ፳፬፥፮)

፫) ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሳል፤ ሕዝብ እርስ በእርሱ ይለያያል። አንዱ መንግሥትም ሌላውን መንግሥት ሊያምነው አይችልም። (ማቴ ፳፬፥፯)

፬) ረሃብ፣ ድርቅ፣ ቸነፈር፣ የምድር መናወጥ በልዩ ልዩ ሥፍራ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ የምጥ መጀመሪያዎች ናቸው። (ማቴ ፳፬፥፰)

፭) በዚያን ጊዜ በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ለመከራ አልፈው ይሰጣሉ ይገደላሉ፤ ስለ ስሙም በአሕዛብ ሁሉ የተጠሉ ይሆናል። (ማቴ ፳፬፥፱)

፮) በዚያን ጊዜ ሰዎች ይሰናከላሉ፤ እርስ በእርሳቸው አሳልፈው ይሰጣጣሉ፣ ይጣላሉ። (ማቴ ፳፬፥፲)

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

**የዓቢይ ጾም አምስተኛው ሰንበት «ደብረ ዘይት» ይባላል።**

፯) ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት መምህራን ይነሳሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ዓመጽ ይበዛል፤ የብዙዎች ፍቅርም ይቀዘቅዛል። በዚያን ጊዜ እስከ መጨረሻው የጸና ብቻ ይድናል ትዕግስትን ያዘወተረ ይድናል። (ማቴ ፳፬፥፲፩-፲፫)

፰) ለአሕዛብ ሁሉ ምስክር እንዲሆንባቸው በሰማያዊው ንጉሥ ፊት ያለምክንያት ለፍርድ እንዲቆሙ የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት ወንጌል በእስላም ቤት ሳይቀር ለሁሉም ይሰበካል። በዚያን ጊዜ መጨረሻው እየቀረበ ይመጣል። (ማቴ ፳፬፥፲፬)

፱) በዚያ ሰዓት በነቢዩ በዳንኤል እንደተባለው የጥፋት ሰው በጽድቅ ሥፍራ የርኩሰት ሰው በተቀደሰው ሥፍራ ቁሞ ይታያል። ክፉ ዲያቢሎስ በሐሳዊ መሲሕ (በአውሬው ሰው) አድሮ የተቀደሰውን ያረክሳል የታነፀውን ያፈርሳል። (ማቴ ፳፬፥፲፭)

፲) በዚያን ሰዓት በከተማ ያሉት ወደ ተራራ ይሸሻሉ፤ በሰገነት ላይ ያለው ደግሞ ከምድር ቤት ያለውን ሊወስድ ሊወርድ አይችልም። በእርሻ ላይ የተሰማራው ገበሬም ወደ ቤቱ ተመልሶ ልብሱን ሊወስድ ጊዜ አያገኝም። በዚያ ወራት ኃጢአትን ለፀነሱ በደልንም ወልደው ለሚያሳድጉ ወዮታ አለባቸው። ሁላችንም ሽሽታችን በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ማለትም ያለፍሬ ሳለን በቅጠል እናርፍበታለን ባልናት በዕለተ ሰንበት እንዳይሆን አጥብቀን ልንጸልይ ይገባል። ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ደግሞ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና፤ ያ የፈተና ጊዜ እግዚአብሔርን ስለሚወዱ ምርጦቹ ባያጥር ኖሮ ሥጋ የለበሰ ሁሉ በሕይወት ባልተገኘ ነበር። (ማቴ ፳፬፥፲፯-፳፫)

፲፩) የበለስ ቅጠል መለምለም ማለት የጠፋችው እስራኤል መንግሥት መመሥረት የመድኃኒታችን መምጣት ፲፩ኛ ምልክት ነው። (ማቴ ፳፬፥፴) ከዚያ በኋላ እኛ በማናውቀው ጊዜና ሰዓት እግዚአብሔር ወልድ በግርማ መለኮት በክበበ ትስብእት (በአካላዊ መጠን) ከቅዱሳን መላእክት ጋር ከደመና ጋር ይመጣል። ዓይን ሁሉ፣ የወጉትም ያዩታል፤ የምድር ወገኖች ሁሉ የሃዘን ድምጽ ያሰማሉ። (ራዕ ፩፥፯-፰) ኃጥአንን በግራው ጻድቃንን በቀኙ ያቆማል። ጥንቱን የሚያስነሳቸውም በሁለት ዓይነት ትንሣኤ ነው። ኃጥአን ለፍርድ ጻድቃን ደግሞ ለሕይወት ትንሣኤ ይነሳሉ (ማቴ ፭፥፳፱ ። ማቴ ፳፭፥፴፩-፵፮)። ኃጥአንን ይወቅሳል፤ ጻድቃንን ያወድሳል። ኃጥአንን እናንተ እርጉማን ከዚህ ወደ ዘለዓለም ፍርድ ሂዱ ብሎ ያሰናብታል። ጻድቃንን ደግሞ እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን የአባቴን መንግሥት ውረሱ ብሎ የእርሱን መንግሥት ያወርሳቸዋል።

**ቅዱሳን ሰዎች ከተነሱ በኋላ እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ዋጋዎች፥**

- የልቅሶና የመከራ ዘመን ያበቃላቸዋል በሃዘን የተያዘ የዚህ ዓለም ሥርዓት ይሻርላቸዋል። (ራዕ ፳፩፥፬ ። ፳፩፥፲፭-፲፯)
- ባለመበስበስ በክብር፣ በኃይል፣ በመንፈሳዊ አካል ተነስተው ሞትን ይዘብቱበታል። (፩ኛ ቆሮ ፲፭፥፵፪-፵፭)
- የመጣውን ጌታ ለመቀበል ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ። (፩ኛ ተሰ ፬፥፲፮-፲፯)
- ጌታቸውን ፊት ለፊት ያዩታል (፩ኛ ቆሮ ፲፫፥፲፪ ። ራዕ ፩፥፯ ። ራዕ ፳፪፥፬)
- የሚያዩትም ጌታቸውን ወደ መምሰል ይለወጣሉ። (፩ኛ ዮሐ ፫፥፪)
- በቅድስና በጽድቅ ሥራ አጊጠው ወደ በጉ ሠርግ ይሄዳሉ። (ራዕ ፲፱፥፰-፱)
- መንግሥቱን ይወርሳሉ። (ማቴ ፳፭፥፴፬)
- በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም በደስታ ይኖራሉ። (ራዕ ፳፩፥፪-፫)
- ሽልማታቸውን ይቀበላሉ። (ራዕ ፳፪፥፲፪ ። ዳን ፲፪፥፫ ። ፪ኛ ጢሞ ፬፥፪-፫ ። ፩ኛ ቆሮ ፱፥፳፭ ። ፩ኛ ጴጥ ፭፥፬ ። ፊልጵ ፬፥፩ ። ፩ኛ ተሰ ፪፥፲፱)
- በእጅ ባልተሰራ ቤት ውስጥ ይኖራሉ። (፪ኛ ቆሮ ፭፥፩-፪ ። ዮሐ ፲፬፥፪-፫)
- ሁሉም አዲስ ይሆንላቸዋል። (ራዕ ፳፪፥፭)
- በግንባራቸው አዳኝ የሆነው ስሙ ይጻፍባቸዋል። (ራዕ ፳፪፥፬ ። ራዕ ፬፥፫-፲፪)
- እግዚአብሔር ለዘለዓለም አምላክና አባት ይሆንላቸዋል፤ እነርሱም ልጆቹ ይሆናሉ። (ራዕ ፳፩፥፫-፯)
- ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም ጌታ አምላክም በእነሱ ላይ ያበራላቸዋል፤ የመብራት ብርሃን የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ይነግሣሉ። (ራዕ ፳፪፥፭)

**መልዕክት፥**

« … በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጧል … አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለኃጢአት ይታይላቸዋል።» (ዕብ ፱፥፳፮-፳፰)። ሐዋርያው ከዚህ በላይ በተመለከትነው መልዕክቱ መድኃኒታችን ለሁለት የተቀደሱ ዓላማዎች ወደ ዓለማችን ሁለት ታላላቅ ምጽአቶችን እንዳደረገና እንደሚያደርግ ያስገነዝበናል።

**የመጀመሪያ ምጽአቱ፥** ሥጋ በመልበስ ለሰው መስዋእት ሆኖ ሊያድን ለካሳ በፍጹም ትህትና የእኛን ውርደት ተቀብሎ በበረት በመወለድ በሥጋ ማርያም መጣ። በሚሞት፣ በሚሰደድ፣ በሚደክም፣ በሚበረታ፣ በሚራብ፣ በሚጠማ፣ በሚዝል፣ በሚወድቅ፣ ባሕርየ ሰብእ (የሰው ባሕሪይ) መጣ። እንደ አንድ ኃጥእ ሞት እስኪፈረድበት ድረስ ራሱን ዝቅ አድርጐ መጣ። ወንጌለ መንግሥቱን ሊሰብክልን ከሞት ወደ ሕይወት ሊያሻግር በሥጋ ማርያም መጣ። ከአይሁድ ስድብን ታገሠ፤ ኃጥአንን በሽተኞችን ሊያድን በምድር ላይ ተመላለሰ፤ ስለእኛ ተገረፈ፣ ተገፈፈ፣ ተሰቀለ፣ ሞተ ያውም መራራ ለሆነ የመስቀል ሞት ታዘዘ። መርገማችንን ተሸከመ ሞቶ በሦስተኛው ቀን ተነሳ፤ ወደ ሰማይ አረገ በየማነ አብ ተቀመጠ፤ የመጀመሪያው ምጽአቱ መከራን ለመቀበል እኛን ለማዳን ነበር።

**ዳግማዊ ምጽአቱ፥** በግርማ መለኮት በክበበ ትስብእት በፍጹም ጌትነት በኃጥአን (የመጀመሪያውን ምጽአቱን ባልተቀበሉት ላይ) ሞትን ሊፈርድ ዓይን ሁሉ እየተመለከተው በገሃድ ይመጣል። ለምእመናን የሚሆነው ክብርም ያን ጊዜ ይገለጣል፤ ኃጥእ ያፍራል ጻድቅ ይከብራል። ሞት ይሻራል፤ ሕይወት ይነግሳል። ሰው (ጻድቅ) ሁለተኛ ላይሞት ይነሳል፤ የምድር ሥርዓት ይሻራል ፍጥረት ሁሉ አንድ መንጋ ይሆናል በአንድ እረኛ ይሰማራል።

ወገኖቼ ክርስቲያኖች ሆይ፥ የመድኃኒችን ሁለተኛ መገለጥ ለእኛስ ለምን ይሆን? ለዘለዓለማዊ ሕይወት ወይስ ለዘለዓለም ሞት?

ጌታ እግዚአብሔር ከሞት ያድነን። በሞት የማይሻረውን ሕይወት ይስጠን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።